# የመምሬ አሰፋ መኮንን የሕይወት ታሪክ

"ኩሉ በከመ ከፈሎ ወከመ ጸውኦ እግዚአብሔር ከማሁ የሀሉ"(፩ኛ ቆሮ. ፯፥፲፯)

"ሁሉም እግዚአብሄር ባዘጋጀለት ተልእኮ ይኑር"

ከቀሲስ አስተርአየ ጽጌ የተበረከተ

የካቲት ፪ ቀን: ፳፻፬ ዓ.ም.



# የመምሬ አሰፋ መኮንን የሕይወት ታሪክ

"ኵሉ በከመ ከፈሎ ወከመ ጸውኦ እግዚአብሔር ከማሁ የሀሉ"(፩ኛ ቆሮ. ፯፥፲፯)

"ሁሉም እግዚአብሄር ባዘጋጀለት ተልእኮ ይኑር"

ከቀሲስ አስተርአየ ጽጌ የተበረከተ

የካቲት ፪ ቀን: ፳፻፬ ዓ.ም.

## መግቢያ

ከግብአተ መሬት በኋላ በመቃብር ላይ መነበብ ያለበት ዜናሕይወት ለፖለቲካ መሪ በዘመኑ የፈጸማቸው ክፉና ደግ ሥራዎቹ፤ ዳኛ ከሆነ በሚዛናዊ ፍርዱ፤ ወታደር ከሆነ አገር ለመታደግ የፈጸመው ጀብዱ፡ አራሽ ገበሬ ከሆነም መልካም ግብርናው፤ የቤት እመቤት ከሆነች ባልትናዋ፡ እናትነቷ፡ ጥበቧና የህይወት ምንጭነቷ፡ በማነኛውም አገልግሎት ተሰማርተው በመልካም የፈጸሙ ሁሉ፡ የፈጸሙት መልካም ተግባር እየተዘረዘረ ከነ እገሌ ከዚህ መንደር ተወለዱ እየተባለ ይነበብላቸዋል።

የካህናት ዜናእረፍት ግን በስሜ አጥምቁ ባለው መሰረት ያጠመቁትን ሁሉ ስሙን ከክርስቶስ ጋራ በማወራረስ፡ ዘሩን በሱ በኩል እንዲቆጥር በማስተማር ሲፈጽሙ የኖሩትን ተልእኮ የሚያንጸባርቅ: ፍጥረትን በየወገኑና በየዘመዱ በፈጠረው በእግዚአብሄር ግብርና በቆሙባት በኦርቶዶክሳዊት ነገረ መለኮትና አስተምህሮ ላይ መመስረት አለበት።

በዚህ ግንዛቤ የአንጾኪያው ኦርቶዶክሳዊው ሊቅ ዮሐንስ የተባለው ካህን "ዝንቱ ውእቱ እምነትነ በአኀጽሮ ዘተምህርናሁ እምትምህርተ አበዊነ ንጹሐን ሐዋርያት ወአበው ጻድቃን እለ አልቦሙ ነውር። ወበዝንቱ ሃይማኖት ተጠመቅነ ወቦቱ ተሐጸነ ወልሕቅነ ወቦቱ ከመ መሰረተ ኮኩህ ጽኑእ ዘኢያንቀለቅል ተሐነጽነ"(፱፫፡፳) ማለትም፡-"የተጠመቅንባት እየተማርን ታንጸን ያደግንባት በእውቀት፤ በማስተዋልና በመንፈስ የጎለመስንባት ያረጀን ያፈጀንባት እምነታችን ይህች ናት" ሲል የተናገረውን የመምሬ አሰፋ ዜና እረፍት ያንጸባርቃል።

"በሰማይና በምድር ሥልጣን ተሰቶኛልና ሂዱ እያስተማራችሁ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እያጠመቃሁ ደቀ መዝሙሬ አድርጉ ባለው መሰረት" ወልደኢየሱስ፡ ዘርአክርስቶስ፡ ወለተሥላሴ እያሉ ሲያጠምቁ የኖሩ እንደ መምሬ አሰፋ ያሉ ታላቅ ካህን፤ በመቃብራቸው ላይ የሚነበብላቸው የህይወት ታሪክ፤ ከአባታቸው ከእገሌ ከናታቸው ከእገሊት ተወለዱ ተብሎ አይጀመርም።

"ኢይቤሎ ለከ ወለአዝርእቲከ ከመ ዘለብዙኃን ዘእንበለ ከመዘለ አሐዱ ለዘርእከ ዘውእቱ ክርስቶስ"(ገላ ፫፡፲፮) የሚለውን የቅዱስ ጳውሎስን መልእክት ተርጉመው ሲያስተምሩ የኖሩ ካህን፤ ከዚህ ጎሳ: ከዚህ ዘር፡ ከዚህ መንደርና ክፍለ አገር መጡ ተብሎ ሊነበብ አይገባም። የምምሬ አሰፋ ዜናእረፍት፤

ሐዋርያት ባስተማሩት ሊቃውንት በተረጎሙት ተመስርቶ ሲያስተምሩ በኖሩት ከዚህ በተቻ በተገለጸው ተጀምሮ በተዝካራቸው ይደመደማል።

እግዚአብሄር በበዘመዱ ወበበ ነገዱ ብሎ ሰውን እንደሌሎች እንስሳት አልፈጠረውም። የምትመስለው እንፍጠርለት ብሎ ሄዋንን ቢያመጣትም ከራሱ አካል ነው። ሰው ከፍጥረታት ተልእኮ በላይ ከፍ ያለ ተልእኮ ስላለው ፤ "በአርያነ ወበአምሳሊነ" (ዘፍ ፩፥፳፮) ብሎ በራሱ አርአያ ፈጠረው። በነብርና በአንበሳ በጅብና በአህያ በበግና በፍየል በአይጥና ድመት በእባብና በአሳ መካከል ያለ አይነት ሩቅ ልዩነት በሰው መካከል የለም። ሰው አካሉ ከምድር አፈር በመምጣቱና በመጨረሻም ወደ ምድርም የሚመለስ በመሆኑ "ለታብቁል ምድር" ተብላ ምድር ካፈራቻው ፍጥረታት ጋራ ተወራረሶና ተደጋግፎ በምድር ቢኖርም፤ የፈጣሪን አርአያና ምሳሌ ተካፋይ በመሆኑ፡ ምድር ካበቀለቻቸው ፍጥረታት ይልቅ ዝምድናውና መምሰሉ ወደ እግዚአብሔር ይቀርባል።

"ምድርን ሙሏት" በተባለ ትእዛዝ የሰው ዘር እየሰፋ ምድር እየጠበበች በተለያዩ ነገዶች ዘመዶች ቋንቃና ባህል እየተራራቀ ቢሄድም፤ እንደ ኢትዮጵያ ባለች ባንዲት ትንሽ አገር ላይ ተዋልዶና ተዛምዶ የኖረው ህዝብ ቀርቶ፤ በዓለም ያለው ህዝብ ሁሉ አንድ ነገድና ዘመድ ነው። ሰው የተጠራለትን ምድራዊ ተልእኮውን የሚፈጽምበት መንገድ ተመሳሳይ ባይሆንም፤ በተፈጠረበት መለኮታዊ አርአያ እና "ባንተ ሊደረግብህ የማትፈልገውን በሌላው ላይ አታድርግ" በሚለው ሐረግ በተጠቃለሉት በ፲ቱ ቃላት አንድ ነው። በዚህም ሰው በየነገዳቸው ከተፈጠሩት ከእንስሳት ፈጽሞ የተለየ ነው።

አርቶዶክሳውያን ሊቃውንት እነ ዮሐንስ አፈወርቅ "ለምንት ኢይቤ እምሕላዌነ ነስአ፤ አላ ይቤ ነሥአ ለህላዌነ ከመ ብእሲ ዘተኀጥአ ፍቅሩ ወሮጸ ለሀሚሥቱ እስከ ረከቦ፡ ወነሥኦ ህላዌ ዚአነ ተኀጥአት እምእግዚአብሄር፡ ወርህቀት እምኔሁ ጥቀ ወሮጸ ድኅሬሃ እስከ ረከባ ወነሥኣ፡ ወይእቲኒ ተወክፈቶ ወክሱተ ግብሩ እስመ ውእቱ ገብረ ዘንተ በአፍቅሮቱ ኪያነ"(ሃ.አ ምዕ ፷፪፡ ፪__፩) እንዳሉት፡ ማለትም፡- "እግዚአብሄር ሰውን መጀመሪያ በምድር ካሉት ፍጥረታት ለይቶ በአርያውና በአምሳሉ እንደፈጠረው ሁሉ፡ ሲጠፋበት ፈለገው። ሲወድቅም እሱን መስሎ ደግፎ ረድቶ ከወደቀበት አነሳው" በዚህም ሰው ከመላእክትም ይለያል።

ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበራቸውን የዘመን አቆጣጠራቸውን ችላ ብለው፤ የምህረት አመት ብለው በክርስቶስ ሥጋዊ እድሜ አቆጣጠር እንደጀመሩ፤ እንደ መምሬ አሰፋ ያሉ ታላላቅ ኢትዮጵያውያን ካህናት እድሜያቸውን መቁጠር የሚጀምሩት ክህነታዊ ተልዕኳቸውን ከጀመሩባት እለትና አመት ነው። በዚህ ግንዛቤ የመምሬ አሰፋ ዕድሜ ፺፮ መሆኑ ቀርቶ ፷፫ አመት መሆኑ ነው ማለት ነው ።

የተቀደሰው ኦርቶዶክሳዊው አስተምህሯችን "ወረሰዮ አሐደ ምስሌሁ በማኅጸነ ዚአሃ ዘቦ ፩ዱ አካል ዝንቱ ዘሰበከ ቦቱ ለድንግል ገብርኤል መልአክ ዘተአመነ ዲበ ምሥጢር ዐቢይ እንዝ ይብል ሰላም ለኪ እግዚአብሄር ምስሌኪ"(ሃይ. አበው. ም.፹፮፡ቁ፮) የሚለውን በመመርኮዝ፡ ማለትም፡- "መለኮታዊ ባህርይው ከኛ ባህርይ ጋራ በማህጸኗ አዋሀደው ይህን ምሥጢር የታመነው ገብርኤል ለድንግል ሰበከ ብሎ

ቅዱስ ሳዊሮስ የተናገረውን ምስክርነት ለማንጸባረቅ፤ ከክርስቶስ ጋራ የተወራረሱበት የክርስትና ስማቸው <u>ዜና ገብርኤል</u> ተባለ።

እነ ቅዱስ ዘካርያስ "እስመ ይእቲሰ እንከ በብሥራተ ገብርኤል መልአክ በጸጋ መንፈስ ቅዱስ ጸንሰቶ ወወለደቶ ወተቀደሰት ቦቱ"(፲፰፡ ፰) እያሉ የሰበኩትን ማለትም፡- እሷስ በቅዱስ ገብርኤል ብስራት አማካይነት በግብረ መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን ጸነሰችው። ወለደችው። እሱን በመውለዷም ተቀደሰች የሚለውን የኦርቶዶክሶችን እምነት በስማቸውም በግብራቸውም ሲመሰክሩ ኖረዋል።

እነ ያዕቆብ ሥሩግ "እምሰማይ ወረድከ በፈቃድከ መሕጸነ ድንግል አግመረከ። ንስቲት ወለት ወለቶሙ ለነዳያን ጾረተከ ገሊላዊት ሀቀፈተከ ነፍሳ ቀደስከ ወሥጋሃ አንጻህከ አጽናእካ ወኢደንገጸት ብከ" (ቅዳ ገጽ ፫፻፵፩፡ ቁ፹፩) ማለትም፡- "በፈቃድህ ከሰማየ ሰማያት ወርደህ በማህጸኗ አደርክ። ይህች ከድሆች ቤተሰብ የተወለደች ብላቴና ገሊላዊት ተሸከመችህ አቀፈችህ ነፍሷን ቀደስክ ሥጋዋንም አነጻህ አጸናህት" እያሉ በመቀደስ ሥጋውን ደሙን እያቀበሉ ካለፉት ታላላቅ ክህናት መካከል አንዱ የቤተክርስቲያናችን ቅርስ ነበሩ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ካህን "ወለነሰ ዘውስተ ሰማያት ሀገርነ"( ፊል፫፡ ፳) የሚለውን ሐዋርያዊ ትውፊት ምሳሌ በማድረግ፡ ማነኛውም የተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ልጅ ምድራዊ ዜግነቱን ሳይለቅ፡ በመንፈሳዊ ዜግነቱ ላይ እንዲያተኩር ያስተምራል። "ኢይከውነክሙ ትቅስፉ ሰብአ ሮሜ ዘእንበለ አበሳ"(የሐ ፳፪፡ ፳፭)። ሲል ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረውን በመከተል፡ የቤተ ክርስቲያን አካል የሆነ ዜጋ ሲታረድና ሲቃጠል እንዳላየና እንዳልሰማ ዝም ማለት ቀርቶ: የፈለገውን እምነት የሚከተል ኢትዮጵያዊ ዜጋ በተዛባ ፍርድ እንዳይበደል ተግተው ይጸልያሉ። በሙሉ ልብ ያስተምራሉ። ለመምሬ አሰፋ ክህነታዊ የህይወት ታሪክ መግቢያ ትሆነኝ ዘንድ እስከዚህ የገለጽኳትን እዚህ ላይ ገትቼ፤ አከናውነው እንዲያልፉ የተጠሩበትን የተልእኳቸው ዝርዝር ከዚህ በታች በገለጽኳቸው አንቀጾች ባጭር ባጭሩ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

፩ኛ፡ "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም" ( ዘፍ ፪፡ ፲፰)

፪ኛ፡ "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት" (ዘፍ ፩፡ ፳፰)

፫ኛ፡ "እያንዳንዱ በተጠራበት ይመላለስ" (፩ኛ ቆር ፯፡ ፲፯)

፬ኛ፡ "ጥረህ ግረህ ኑር" (ዘፍ ፫፡ ፲፱)

፭ኛ፡ ተዝካር

፮ኛ፡ አማረኛ ቅኔ

ወደዘረዘርኳቸው አንቀጾች በመሻገር ባንደኛው አንቀጽ ሀተታየን እጀምራለሁ።

# ፩ኛ፡ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም።

ክህነት የምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን ማስፈጸሚያ መሳሪያ ስለሆነ በምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን ላይ መመሥረት አለበት። ከምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን ዋናውና ተቀዳሚው እግዚአብሄር "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም" ( ዘፍ ፪፡፲፰) ብሎ ተፈጥሮን የካነበት የህይወት ምንጭ (ፈልፈለ ሕይወት) የሆነው የተፈጥሮ ህግ ጋብቻ ነው። ይህ ህይወትን ለማመንጨት ከፈጣሪ ለፍጡራን የተሰጠ የተፈጥሮ ክህነት የሆነው ጋብቻ የተመሰረተው በሁለት ተቃራኒ ጾታዎች በሴትና ወንድ ጥምረት ላይ ብቻ ነው።

ይህ ህይወት ላለው ለዕጸዋት ሳይቀር የተሰጠ ተፈጥሮአዊ ክህነት፤ ልጅን ከናትና አባት ለይቶ፡ ወንዱን ከማያውቃት፡ ሴቷን ከማታውቀው አካል ጋራ ጎትቶ የሚያጣብቅ ረቂቅ ኃይል ነው። ቅዱስ ጳውሎስ "ዓቢይ ውእቱ ዝ ነገር" ማለትም "ረቂቅ ምሥጢር ነው" ብሎታል (ኤፌ ፭፡፴፪)። <u>**መምሬ** **አሰፋ** ይህችን ዓለም አቋርጠው እንዲሄዱባት የተጠሩላት ተልእኳቸውን የፈጸሙበት ቅስና የተመሰረተችው በዚህ ረቂቅ ምሥጢር ላይ ነው</u>።

የመምሬ አሰፋ ክህነት "የአንዲት ሚስት ባልና ልጆች ያሉት"(፩ኛ ጢሞ. ፫፥፪) በሚለው ረቂቅ መስፈርት የተሰፈረች ናት። በዚህ ረቂቅ ኃይል ላይ የምትመሰረተው ሲመተ ክህነት "ከእንጨት መርጦ ለታቦት ከሰው መርጦ ለሹመት" እንዲሉ "አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሲመቱ ለመልከ ጼዴቅ" (ዕብ ፭፥፮) በሚለው እንደ መልከ ጼዴቅ ከተባለችው ክርስቶሳዊት ክህነት ጋራ የተያያዘች ናት። ይህች ኦርቶዶክሳዊት ክህነት በብዙ ራዕይና ጥንቃቄ በተመላው ምርጫ የምትሰጥ <u>የክርስቲያኖች ህልምና ራዕይ የመሰክሩላት መሆን ይገባታል</u>።

በዚህ ቅዱስ ባህል ላይ የተመሰረተችው ኦርቶዶክሳዊቷ የመምሬ አሰፋ ክህነት በተከበሩ ባለቤታቸው እናትና አባት ራዕይ ተገለጠች። ተመሰከረላትም። መምሬ አሰፋን ገና ያላወቁ የመምሬ አሰፋንም የ፷፰ ሲመተ ክህነት በእቅፋቸው በነበረችው ብላቴና ህይወት ውስጥ አሻግረው አዩዋት። ለመምሬ አሰፋ ክህነታዊ ተልእኮ ወጋግራና ምሰሶ ሆነው ለማስፈጸም በተካፋይነት እግዚአብሄር ያዘጋጃቸውን ለ ፸፪ አመታት አብረው ኖረው በሞት የተለዩዋቸውን ክብርት ባለቤታቸውን ገና በናታቸው እቅፍ ሳሉ <u>**የሹምነሽ**</u> ብለዋቸዋል።

የባለቤታቸው ስም <u>**የሹምነሽ**</u> ፤የሳቸውን ታላቅ ሲመተ ክህነት ለመግለጽ በትንቢት የተሰጠች እንደነበረች ሁሉ ፤ የልጅ ስምም ያባትን ባህርይ ገላጭ ነውና የሳቸውን ምግባርና ባህርይ ለመግለጽ <u>**መላኩ**</u> የሚለውን መልካም ቅጽል የሌንጮ ማርያም ህዝብ በሰጧቸው ወቅት ለተወለደው ልጃቸው መጠሪያ ስሙ ሆኖታል። በተቀደሰችው ክህነታቸው በይርጋ ዓለም ከተማ ላበረከቱት ሁሉ ምግባረ ሠናይ መታሰቢያ ይሆናቸው ዘንድ ለወለዷት ልጃቸው የይርጋ ዓለም ህዝብ <u>**መልካም ሥራ**</u> ብሎ ሰይሚታል። ስም ካነሰሁ ዘንዳ ከወለዷቸው ፭ ወንዶችና ፭ ሴቶች ለምሳሌ ያህል አንድ አንድ አንድ ጠቀስኩ እንጅ አሥሩ ሁሉ የሚጠሩባቸው ስሞች የሳቸውን ተልእኮ የሚገልጹ ናቸው።

ይህች ክህነት ዘመነ መንሱት ባፈራቸው ጳጳሳት በአንብሮ እድ ተሰይሞ ከሚታወጀው ክህነት ፈጽማ የተለየች ናት። ክህነት ከዓለም ፍላጎት ሸሽቶና አምልጦ በገዳም ተወስኖ ለመኖር በግል ፈቃድ ከሚሸከሙት ምንኩስናም ፈጽማ ትለያለች። ክህነት የህዝብ መገልገያ የህዝብ ንብረትነት ያላት ህዝባዊት ስለሆነች በህዝብ ጥያቄና ትእዛዝ ጳጳስ በአንብሮ እድ ያውጃት እንጅ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ክህነት የምትፈልቀው ከህዝብ ነው። የመምሬ አሰፋ ክህነት በሥጋና በመንፈስ ውህደት ላይ የተመሰረተች "ብዝሁ ወተባዝሁ ወምልዕዋ ለምድር" ብሎ ፈጣሪ ያዘዘውን ተልእኮ በሥጋና በመንፈስ የፈጸመች ክህነት ናት።

## ፪ኛ፡ "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት" (ዘፍ ፩፥፳፰)

በዚህ ረቂቅ ምሥጢር ላይ የተመሰረተችውን ክህነት የባለቤታቸው የወይዘሮ የሹምነሽ እናትና አባት አስቀድመው ተገንዝበው የጋብቻን ምሥጢር በተግባር እያከናወነች ህዝብ ለምታገለግለው <u>ለመምሬ አሰፋ ክህነት የተፈጠርሽ ነሽ ከተባለችው ብላቴና</u> ጋር በመሰረቱት ጥምረት፤ ከ፲፱፻፷፯ ዓ/ምህረት ጀምሮ እስከ ፲፱፻፺፱ አብኖረው በኖሩበት ዘመን፤ "ብዝኁ ወተባዝሁ ወምልእዋ ለምድር" ብሎ ፈጣሪ የሰጠውን ትእዛዝ ፈጽመዋል። በዚህ ህገ ተፈጥሮ ያበረከቱትን ተልእኮ የበለጠ ግልጽ ለማድረግ፡-

፩ኛ፡- ከራሳቸው አብራክ በፈለቁት ፲ ልጆቻቸው "ብዝኁ" የሚለውን

፪ኛ፡- ከወለዷቸው ልጆቻቸው በተወለዱት ፴፬ የልጅልጆቻቸው "ተባዝሁ"

፫ኛ፡- ከልጅልጆቻቸው በተወለዱት ፷ ልጆቻቸው "ምልእዋ ለምድር" የሚለውን ትእዛዝ ፈጽመዋል።

ይህችን አለም ለመልቀቅ በተቃረቡበት ወቅት የተወለዱትን ወንዱን <u>እሼቴ፤</u> ሴቷን <u>የዓለም ፍሬ፤</u> ብለው ሰየሟቸው። በፍጻሜ ዘመናቸው ለመጡት ሕጻናት በሰጧቸው ስሞችም "ወትሬእይ ውሉደ ውሉድከ ወትበልእ ክራማቲከ"(ዘዳ ፳፰፡፪፯) ተብሎ ለእነ አብርሃም ይስሀቅና ያዕቆብ የተሰጠው በረከትና ጸጋ መታደላቸውን መስክረው ያለፉ በሁሉ የተባረኩና የታደሉ ታላቅ ካህን ናቸው።

## ፫ኛ፡ "እያንዳንዱ በተጠራበት ይመላለስ" (፩ኛ ቆር ፯፥፲፯)

"ወይደልዎሙ ለቀሳውስት ከመ ይኩኑ በአምሳለ ሊቃናት ዘናሁ ኀለፉ እምወሰነ አሐቲ ብእሲት ከመ ይሳተፉ ምሥጢራተ" (ፍ. አ. ፯፥፪፻፲፯) ማለትም፡- "የቅስናን ተልእኮ ለማከናወን የሚሰየሙ ሰዎች እንደ መጀመሪያዎቹ ቀሳውስት ባንዲት ሴት የተወሰኑ መሆን ይገባቸዋል" ለሚለው ህግ ተገዥ በመሆን ከወይዘሮ <u>የሹምነሽ ቸሩ</u> በተፈጥሮ ክህነታቸው በሥጋ ከወለዷቸው ፷፬ ልጆቻቸው ጋራ ጎን ለጎን

በ፲፱፻፴፮ ዓ/ምህረት በተቀበሉት ቅስናቸው "ወእመሰ አዕላፈ አምህርተ ብክሙ፤ አበዊክሙሰ በክርስቶስ ኢኮኑ ብዙሐነ እስመ አነ ወለድኩክሙ በትምህርተ ኢየሱስ ክርስቶስ"(፩ኛ ቆሮ ፬፡፲፭) እያሉ ብዙ የመንፈስ ልጆች ወልደዋል። በዘመኑ ከነበሩት ታላቁ መንፈሳዊ አባት ከአቡነ ጢሞቴዎስ ጋራ ፲፱፻፵፬ እስከ ፲፱፻፶፫ ዓ/ ምህረት በይርጋ ዓለም ዙሪያ በነበሩት ሶስቱ አብያተ ክርስቲያናት በስብከተ ወንጌል እና የማረሚያ ቤት መምህረ ንስሀ በመሆን ለ፲፩ አመታት አገልግለዋል።

<u>በአቡነ ጢሞቴወስ ቡራኬ ግንቦት ፲፱ ቀን ፲፱፻፵፰ ዓ.ም. የአዋሳን ደብረ ምህረትን የቅዱስ ገብርኤልን ጽላት በመቃኞው አስገብተው</u> ለአባ ኃይሌ አወቀና ለመምሬ ወንድሙ መኮንን በመቃኞ ይካሄድ የነበረውን አገልግሎት አስረክበው ወደ ቋሚ አገልግሎታቸው ወደ ይርጋ ዓለም ተመለሱ። ከሰባት አመታት በኋላ ከየካቲት ፴ ቀን ፲፱፻፶፭ ዓ.ም. ወደ አዋሳ ተመልሰው ነፍሶቻቸውን ይማርና ከመምሬ መኮንንና አባ ሃይሌ አወቀ ጋራ አገልግሎት ጀመሩ። በአዋሳ ከተማ ለ፵፩ አመታት ሲያገለግሉ ቆይተው ይህን ረዥም ያገልግሎት ዘመን ያደላቸውን እግዚአብሄር በምንኩስና ለማመስገን በ፲፱፻፺፮ ሚያዝያ ፱ ቀን ከባለቤታቸው ከወይዘሮ የሹምነሽ ጋራ ሥርአተ ምንኩስና ፈጸሙ።

እስኪ መነኮሱና አዲሱ ሕንጻ ስራው ተፈጽም አገልግሎት እስኪሰጥ ድረስ ከኮርያ ዘምተው ለተመለሱ በተሰራው በቀድሞው ህንጻ ለ፵፩ አመታት በቅስና አገለገሉ። ይህን እድል ለሰጣቸው አምላክ በምንኩስና ለማገልገል ከገቡት ብጽአት ጋራ የተጀመረውን ህንጻ ተፈጽሞ ለማያት ባላቸው የጋለ ፍላጎት፡ የህንጻው መሰረት ከተጣለበት ከ፲፱፻፸፯ አ/ምህረት ጀምሮ ተፈጽሞ አገልግሎት እስኪጀምር ድረስ፤ ለ፲፱ አመታት በየወረዳዎች እና አውራጃዎች እየተዘዋወሩ፡ ከቤታቸው ሌሊት ወጥተው ሌሊት በመግባት፡ አንዳንድ ጊዜም ከቤታቸው እንደወጡ በመዋል በማደር ከሰውነታቸው ሳይወልቅ የሰነበተው ልብሳቸው የበርሀ ባህታዊ አስመስሏቸው፤ ሥጋቸው አልቆ፡ አጥንታቸው ደቆ፡ ቆዳቸው ጠውልጎ ይመለሱ ነበር።

ያገኙትን ገንዘብ በዕቁብና በማንኛውም በሚበረክትበት እያባዙ ባበረከቱት ገንዘብ ህንጻው ተፈጽሞ ለምረቃ እንዲበቃ ካደረጉት አባቶች በዋናነት ከሚጠቀሱ አባቶች አንዱ እንደነበሩ ከግብአተ መሬት በኋላ በተነበበው የህይወት ታሪካቸው ላይ ተመዝግቧል።

በጥቅሉ በሥጋ የወለዷቸውን አስተምረው ከማሳደግ ጋራ ከዚህ በላይ የተገለጸውን ሁሉ ተልእኮ ለመፈጸም ባደረጉት ጥረት "ጥረህ ግረህ ኑር" (ዘፍ ፫፥፲፱) የሚለውን በትክክል የፈጸሙ መስተጋድል ታላቅ አባት ናቸው።

# ፩ኛ "ጥረህ ግረህ ኑር" (ዘፍ. ፫፡፲፱)

በናት ማህጸን ተጥለፍልፎ የተጀመር ህይወት የተጥለፈለፈ የእድገት ጉዞውን ጨርሶ በተጥለፈለፈ ሞት በማህጸነ ምድር ያልቃል። ሰው በተጠራለት ተልእኮ ላይ ጸንቶ በመቆም የተጠራላትን ተልእኮ እየሞተና እየተወለደ ይፈጽማል።በዚህ አይነት ረቂቅ ሂደት የሰው ህይወት ካንድ እርከን ወደሌላ እርከን የመሸጋገሪያ የእድገት ድልድዮች አሉት። እነዚህም ሥጋውያንና መንፈሳውያን ልደቶችና ሞቶች ናቸው።

ለመሞት መወለድ አለበት። ለማደግም ደግሞ መሞት አለበት። ይህን የተፈጥሮ ውስብስብ ህግ ለመፈጸም ሰው በተለይም ክርስቲያን የሆነ ሰው ሶስት ጊዜ እየተወለደና እየሞተ ያድጋል።

፩ኛ የመጀመሪያው ሞትና ልደት፡- ተፈጥሮ እንደ ሰረዝ ቅኔ ጥልፍልፍ ወይም ውስብስብ ነው። የመጀመሪያው ሞት በናት ማህጽን በሚያስደንቅ ሚስጢር ተጸንሶ የተወሰነለትን የእድገት ወራቱንና ደረጃውን ጨርሶ ወደ እዚህ ዓለም ሲመጣ ነው። በውስብስ ተፈጥሮ ለ፱ ወራት ከኖረበት በኋላ ለእናቱ ማህጸን ሞቶ ለዚህች ዓለም ይመጣላታል። ለተለያት ለናቱ ማህጸን ግን ሞተባት።

፪ኛ ሁለተኛ ሞትናልደት፡- ከክርስትና ክልል ውጭ ያሉት ሰዎች የማይጋሩት በክርስቲያኖች ብቻ የሚፈጸመው ጥምቀት ነው። “አእምሩ ኩልክሙ ከመ እለ ተጠመቅነ በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ውስተ ጥምቀት ሞትነ ወተቀበርነ ምስሌሁ ከመ ክርስቶስ ተንሥአ እምውታን በስብሀተ አቡሁ ከማሁ ንሕነኒ ናንሶሱ ውስተ ሐዳስ ሕይወት ” (ሮሜ ፮፡፫÷፭) እንዳለው፡ “ጥምቀት፤ ለናታችን ማህጸን ሞተን፤ በሥጋ ተወልደን ወደ ዚህች ዓለም ከመጣን በኋላ፡ ከክርስቶስ ጋራ ሞተን በመነሳት፤ ክርስቶስ ከሚጠላቸው ነገሮች ራሳችንን ለይተን፤ ለዘላለም የምንኖርባት ክርስቲያናዊት ህይወት ናት።”

፫ኛ ሶስተኛው ሞትናልደት፡- ነፍስና ሥጋ ተለያይተው በርደተ መቃብር የሚፈጸመው ነው። ይህ የመጨረሻው ልደትና ሞት ከሌሎቹ ሞቶችና ልደቶች እጅግ የረቀቀ ስለሆነ ከበድ ይላል። በዚህ ሞትና ልደት ሰው የመጨረሻውን ሞትና ልደት ሲፈጽም የሚለያየው ከሚወደው ወገን ብቻ ሳይሆን፤ ሥጋው ከነፍሱ፡ ነፍሱ ከሥጋው በመለየት ጭምር ነው። ለዚህ ዓለም ማህጸን ሞቶ፡ ለሚመጣው ረቂቁ አለም ሲወለድ ምጡን እጅግ ያሰፋዋል። ሰው የዚህን ዓለም ጥልፍልፍ ሕይወት ፈጽሞ በሞት እስኪለይ ድረስ በሚያከናውናቸው ክፉና ደግ ተግባሮቹ አብሮት በተንቀሳቀሰው ሰው ህሊናና ስሜት ተጸንሶ ተረግዟልና፤ ለዚህ ዓለም ሞቶ፡ ለሚመጣው ዓለም ሲወለድ፡ ምጡ እጅግ ሰፍቶ የሁሉም ይሆናል።

መምሬ አሰፋ በ፲፱፻፱ ዓመተ ምህረት ግንቦት ፲፱ ቀን ሲወለዱ በምጥና በግአር የጀምሩትን ምድራዊ ሕይወት፡ በተወለዱ በ፺፮ አመታቸው ታህሳስ ፳፪ ቀን ፪ሺ፭ ፈጸመው ሲለዩ በሥጋና በመንፈስ ለወለዷቸው ልጆቻቸውና አብረዋቸው ለኖሩት ወኅኖቻቸው ሁሉ ምጥና ገአር ሆኗል። ሰው ወገኑ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለየው የሚያይበትንና የሚዳሰስበትን አካሉን ወደ መቃብር ከሸኘ በኋላ፡ ለመዘከርና ለማየት የሚሞክረው ጥልፍልፏን ምድራዊት ህይወት ጀምሮ እስኪ ፈጽማት ድረስ አትርፎት በሄደው ተግባር ነውና፤ መምሬ አሰፋ እንዲታሰቡ የሚያደርጓቸውን አባይት ተግባራት በመጥቀስ ዜና ህይወታቸውን በመታሰቢያቸው (በተዝካራቸው) እደመድማለሁ።

# ፫ኛ ተዝካር (መታሰቢያ)

“ኵሉ በከመ ከፈሎ ወከመ ጸውአ እግዚአብሔር ከማሁ የሀሉ”(፩ኛ ቆሮ. ፯፡፲፯) ማለትም “ሁሉም እግዚአብሄር ባዘጋጀለት ተልእኮ ይኑር” እንደተባለው፡ ሰው የህይወት ዘመኑን ሲኖር የሚያደርገውን ጥረት ለማከናወን የየራሱ ተልእኮ (ሙያ ችሎታ) አለው። በዚህ ዓለም የነበረውን ምድራዊ ተልእኮ ፈጽሞ በሞት ሲሰናበት፡ ከሰውነቱ ካመነጫቸው ልጆቹ ጀምሮ በተሰማራበት ሁሉ የፈጸማቸው የማይረሱ ተግባራቱ ናቸው።

ስለ ተዝካር ከዚህ ቀደም ጥቅምት ፳፱ ቀን ፳፻፫ ዓ/ምህረት ተዘጋጅታ በቀረበችው ጦማር ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በዚህች ጦማር ግን ሳይዋሹ ቃላቸውንና ተልእኳቸውን ሳይለዋውጡ ምእመናን ሳያታልሉ የተቀደሰች ሩጫቸውን ፈጽመው ላለፉ መምሬ አሰፋን ለመሰሉ ታላላቅ ካህናት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን የምታስተምረውን ተዝካር (መታሰቢያ) መግለጽ እፈልጋለሁ።

ቅዱስ ጳውሎስ “ወተዘከሩ አኀዊነ ጻማነ ወስራህነ ከመ መአልተ ወሌሊተ ኮነ ንትጌበር ከመ ኢናክብድ ላዕለ አሐዱሂ እምውስቴትክሙ” ( ፩ ተሰ ፪፡፰፡፱) ከናንተ መካከል ባንዳችሁ ሸክም እንዳንሆን <u>ሌትና ቀን እየሰራንና እየደከምን ያሳለፍነውን ሥራችንን አስታውሱ</u>” እንዳለው ካህናት በህይወተ ስጋ ሳሉ ሌትና ቀን በመስራት በስንክሳራችን ተጽፎ በቀሪው ህዝበ ክርስቲያን የሚነበብ ቀዋሚ ትዝካር መታሰቢያ ሊኖራቸው ይገባል::

የመምሬ አሰፋን ተዝካር(መታሰቢያ) ከሁሉም ልዩና መታሰቢያነቱን እጅግ ከፍ የሚደርገው ቅዱስ ጳውሎስ ከገለጸው እይነት ባሻገር ከቅድስት ድንግል ማርያምና ከቅዱስ ገብርኤል ተልእኮ ጋራ መተሳሰሩ ነው። ከመላእክት ሁሉ በኢትዮጵያውያን አዕምሮ ፈጥኖ ብቅ የሚለውና ባንደበታችንም ስሙ የሚዘወትረው የቅዱስ ገብርኤል ስም ነው።

የመምሬ አሰፋ ተልእኮ ሊቁ ዮሐንስ የተባለው ካህን “ወበዝንቱ ሃይማኖት ተጠመቅነ ወቦቱ ተሐጸነ ወልሕቅነ ወቦቱ ከመ መሰረተ ኮኩህ ጽኑእ ዘኢያንቀለቅል ተሐነጽነ”(፻፫፡፰) ብሎ የተተናገረውን ኦርቶዶክሳዊውን መርሆ የተከተለ ነው። “የተጠመቅንባት እየተማርን እየታነጽን ያደግንባት በእውቀት፤ በማስተዋልና በመንፈስ የጎለመስንባት ያረጀን ያፈጀንባት እምነታችን ይህች ናት” እንዳለው፤

## <u>መምሬ አሰፋ</u>፡-

፩ኛ፡ **ግንቦት ፲፱ ቀን ፲፱፻፱** ዓ/ምህረት <u>በዕለተ ገብርኤል በመወለዳቸው</u> “ዘሰበከ ቦቱ ለድንግል ገብርኤል መልአክ ዘተአመነ ዲበ ምሥጢር ዐቢይ እንዝ ይብል ሰላም ለኪ እግዚአብሄር ምስሌኪ”(ሃይማኖተ አበው ም ፹፯፡ቁ፯) እንዲል ቅ.ገብርኤል ለቅድስት ድንግል ለእመቤታችን ያቀረበውን ብሥራት የያዘውን ተልእኮ ለማንጸባረቅ <u>ዜና ገብርኤል</u> ተብለው ተሰየሙ።

፪ኛ፡ ግንቦት ፲፱ ቀን ፲፱፻፵፰ ዓ/ምህረት በዕለተ ገብርኤል በተወለዱባት እለት ጽላቱን ወደ አዋሳ መቃኞ ከይርጋ ዓለም አምጥተው ለመምሬ ወንድሙና አባ ኃይል አስረከቡ። ከሰባት አመታት በኋላ ተመልሰው በአዋሳ ከተማ በዚህ በተመቅደስ ለ፵፱ አመታት አገለገሉ።

፫ኛ፡ ግንቦት ፲፱ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ምህረት። በዕለተ ገብርኤል በተወለዱባት ቀን አዲሱ ህንጻ ተፈጽሞ ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ። እነዚህ ሁሉ የመምሬ አሰፋን ተዝካር (መታሰቢያ) ከፍ አርገው የሚያሳዩ ምልክቶች ናቸው። በተለይም ይህች እለት ከሌሎቹ ሁሉ ዕለታት ለመምሬ አሰፋ "እምርት" (የተመረጠች) የተባለችው እለት ነበረች።

ታላቁ ካህን መምሬ አሰፋ ቅስናውን ከተቀበሉበት ጀምሮ ይህችን ዓለም እስከለቀቋት ድረስ ቅዱስ አትናቴዎስ "ኦ ዘታወጽኦ ለህጻን እምሐቆ ብእሲ ወትፌነዎ ውስተ ከርሰ ብእሲት ወትጠበልሎ በሰፋድል ረቂቅ ወእንዘ ማይ ውእቱ በጥበብከ ታረግዖ ወትነፍህ ላዕሌሁ መንፈሰ ሕይወት ወበ ፵ ዕለት ትሰይም ዲቤሁ በዘኮነ ከዊኖ" ብሎ ያዘጋጀውን ቅዳሴ (መ፡ቅ፡ ገጽ ፪፻፴፪፡ ቁ፡፻፲፬) ማለትም፡- ሕጻንን በናቱ ማህጸን ሰርተህ ሰው ለማድረግ መጀመሪያ ከወንዱ ወገብ አፍልቀህ ወደ ሴቷ ማህጸን ዘሩን ትልከዋለህ፡ በሰፋድልም ትጠቀልለዋለህ፡ ውሀ የነበረውን አርግተህ ሰው ታደርገዋለህ፡ በ፵ ቀኑ ለተልእኮው ተሰይመዋለህ" የሚለውን ለ፷፰ አመት እያንጎራጎሩ በ፵ ዕለት ሲጠመቁ የጀመሯትን ተልእኮ ፈጸሙ።

"አበዊነ ወአኃዊነ ወአኃቲነ እለ ኖሙ ወአዕረፉ በርትእት ሃይማኖት ወደምር ነፍሳቲሆሙ ውስተ ህጽነ አብርሃም ይስሀቅ ወያዕቆብ"(ቅ ገጽ ፩፪ ቁ ፹፭) እያልን በቅዳሴያችን በየቀኑ የምንጸልየው ጸሎት የሚያሳየን ቀደም ብለው ያለፉትን የነ አብርሃምን ይስሀቅንና ያዕቆብን እቅፍ በተስፋ እንድናይ የሚያደርገን ነው። መምሬ አሰፋ እድሜ ልካቸውን ሲመኟት የነበረችው ይህች እቅፍ ክርስቶስ ከኛ በሥጋ ተለይቶ ለኛ ያዘጋጅልን ዘንድ የገባባት በሰማይ ያለች የአብ ከተማ ናት። የካህናት ተልእኮ ወደዚህች ከተማ ለመግባት ለተጠመቁ ሁሉ ይህን የመሰለ ተዝካር (መታሰቢያ)ማትረፍ ነው።

"ሕጽን ነፍሶሙ ውስተ መካን ሥዑር ውኅበ ማየ ዕረፍት ውስተ ሕጽነ አብርሃም ይስሀቅ ወያዕቆብ" (መስተብቁዕ በእንተ ሙታን) በሚለው ጸሎት የመምሬ አሰፋ አካል ወደ ግብአተ መሬት ሲሸኝ፡ የመምሬ አሰፋን ተዝካር (መታሰቢ) በአዋሳ ከተማ ህዝብ ብቻ ሳይወሰን በዋይታቸው ያጀቡት ወፎችም ተሳትፈውታል።

መምሬ አሰፋ በ፲፱፻፺፮ ሚያዝያ ፱ ቀን ከባለቤታቸው ከወይዘሮ የሹምነሽ ጋራ የፈጸሙት ምንኩስና የቁም ተዝካራቸው ነበር። ይህ የመምሬ አሰፋ አይነት ምንኩስና (ተዝካር) የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ስርአተ ምንኩስና ነው።

"ወረሲኦ ወፈጺሞ መዋዕሊሁ" እንደተባለው የኦርቶዶክስ ምንኩስና እንደ መምሬ አሰፋ በቅስና ሲያገለግሉ ኖረው የተጓዙበትን የረዥም ዘመን ተልእኮ አጠቃልለው በቀሪው ዘመናቸው በህዝብ ህሊና ላይ የሚያንጹት መልካም ምሳሌ ነው። መነኮሳት ከህዝብ ጋራ አብረው እንዲኖሩ የሚፈቀድላቸው እንደ አባ አሰፋ የህይወታቸውን ተልእኮ ለመደምደም በሚያካሂዱት ዝግጅት ያጠራቀሙትን የተትረፈረፈ በረከትና ጸጋ ሲያገለግሉት ከኖሩት ጋራ በመካፈል ለመደምደም በዝግጅት ላይ ሲሆኑ ብቻ ናቸው። በዚህ መንገድ

ብቻ ካልሆነ በቀር ምንኩስና ከገዳም ወጥቶ ለከተማ ኑሮ ከተጋለጠ ምንጭ እንደሌለው ድንገት ደራሽ ጎርፍ ይደርቅና፡ በሮማ ካቶሊክ ምንኩስና ላይ የደረሰው የመንፈስ ድርቀት ከሰል ያደርገዋል። ለቀሪው ህዝብ የሚያተርፈው ተዝካር ሊኖረው ቀርቶ ያካባቢውን መግባረ ሠናይ እንዳለ ይዞ ት ይሞታል። መምሬ አሰፋ ይህችን ዓለም ከመሰናበታቸው ከወር በፊት ዘመነመንሱት ያሉት ይህን መሳይ ምንኩስና የሚያንጸባርቀውን ዘመን ነው።

በመምሬ አሰፋ መንገድ የመነኮሱ አባቶች በሰው ተከበው በከተማ ቢኖሩም፤ አምባቸውን ግርማሌሊት፡ አነጋጋሪ ጎረቤታቸውን ድምጸአራዊት አድርገው በገዳምና (በምደረ በዳ) ለኖሩት ለነ መቃርስ እና ለአስተርያው መነኩሴ ለአባ ጆርጅ ሜንዴል የተሰጠቸው ከፍጥረታት ጋራ የመነጋገር ስጦት አያመልጣቸውም። አባ ጆርጅ ሜንዴል ራሱን ከዓለም ለይቶ መንኩሶ ግርማሌሊቱን አምባው፡ ድምጸአራዊቱን አነጋጋሪ ጎረቤቱ አድርጎ በስነ ፍጥረት ተመራምሮ ያገኘውን እውቀት (የጀነቲክ) ለተዘካሩ መታሰቢያ እንዲሆነው ለሰው ልጅ አበርክቷል። እነ አባ መቃርስም፡ ማር ይስሀቅ ፊልክስዩስና አረጋዊ መንፈሳዊ በሚባሉት መጻህፍት የሰፈሩትን ምክር ተግሳጽና ትምህርት የሰጡት ተልእኮ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በእውነተኞች ገዳማውያን መነኮሳት ሲታሰቡ (ሲዘከሩ) እንዲኖሩ አድርጓቸዋል።

እንደ መምሬ አሰፋ ያሉ መንፈሳውያን የጥበብ ሰዎች በንፍሳቸው ህያው ናቸው።ከልጅንታቸው እስከ እርግናቸው በፈጸሚቸው ተግባራት ከመቃብር በላይ ናቸው።በነሱም ሲመክሩንና ሲገስጹን ይኖራሉ። እንደነዚህ ያሉ ታላላቅ አባቶች ሰርተው ትተውልን የሄዱት እንደ ኤልያስ አጽፍ፡ በበረከት የተሞላ ዘላለማዊ ቅርስ ነው። በፊታችን የተዘረጋውን ማእበል እንድናቋርጥበት የሚረዳ ኃይል ነው። (፪ኛ፡ ነገ፡ ም፪ ቁ፱__፲፬ )

ይህ መንፈሳዊ ኃይል ቅርሳችን ሆኖ ሊረዳን የሚችለው፤ ኤልያስ ከዚህ ዓለም ሲለይ ወደ ኋላ ለቀረው ደቀ መዝሙሩ ለኤልሳ "በተወሰድኩ ጊዜ ብታየኝ ይሆንልሀል፡ አለዚያ ግን አይሆንልህም"(ቁ ፲) እንዳለው፡ እንደ መምሬ አሰፋ ከሹመት ከግል ዝናና ከጥቅም እራሳቸውን ሰውረው፡ በተጠሩለት የተቀደሰ ምሳሌ ወደ ኋላ ለቀረነው በተውልን ተዝካራቸው (ቅርሳቸው) ውስጥ አተኩረን ስንመለከታቸው ብቻ ነው።

የተውልንን ምሳሌ ለመከተል ፈቃደኞች ባንሆን፡ ተግሳጻቸውን የሚቀበላቸው ሰው ሲያጡ፡ እንደ ታላቁ ነቢይ ኢሳይያስ "ስምኢ ሰማይ ወአጽምኢ ምድር"(፩;፪) ብለው ቅሬታቸውን ለተፈጥሮ ያሰማሉ። ክርስቶስ "እስመ ውሉደ ዝ ዓለም ይጠበቡ በዓለሞሙ" እንዳለው ማለትም፡- ወልዶ ዘር በማትረፍ የህገ ተፈጥሮን ተልእኮ የፈጸሙ፡ እየቀደሱ በማስቀደስ የተፈጥሮ ሚዛናቸውን ጠብቀው በሥጋና በመንፈስ በረከታቸው ተትረፍርፎ የተለዩ የጥበብ ሰዎች በሚያቀርቡት ክስና ወቀሳ ተከሳሽና ተወቃሽ መሆን እራሳቸው መምሬ አሰፋ ይህችን ዓለም ከመልቀቃቸው በፊት ዘመነመንሱት ላሉት ለጥፋት መዘጋጀት ነው።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ "ቦኑ እግዚአብሄር ይፈቅድ ስምዐ ዘእንበለ እመህያው፡ ወይቤ ጎድግሰ ሰብአ፡ ያቀውም ስምአ ሰማየ ወምድረ ወኮኩሐ ለሰሚዕ ዘኢይትናገር"( ሃ፡ ም፡ ምዕ ፰፫፥ቁ. ፴፰)

እንዳለው፡ ማለትም፡- "ህብረተሰብ ተሳስቶ መንገዱን ስቶ በጥፋት መንገድ ሲሄድ ቆም ብሎ እንደነዚህ ያሉ አባቶች መዘክራቸውን ባናይ፡ የተናገሩትን ባንሰማ፤ እግዚአብሄር የመጨረሻ ቁጣውን ከመላኩ በፊት ሰማይንና ምድርን እንጨቱን ድንጋዩን ለምስክርነት ያዘገጃል"።

የአዋሳ ህዝብም ሆነ ይህችን ዜና ህይወት የምናነብ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በመምሬ አሰፋ ርደተመቃብር ከተንጫጩት ወፎች፤ ከጉንዳኑና ከንቡ መስማትና መማር ይኖርብናል። "ሊጠፋ በወሰነ ህዝብ ጆሮ ከበሮ ቢደበድቡበት አይሰማም" ብለው የጥንት አባቶች የሰጡን ከባድ የማስጠንቀቂያ መዘክር (ማሰሰቢያ) የምንዘክርበት ወቅት ነው።

ቤተክርስቲያናችን ብጹአንና ቅዱሳን ብላ በስንክሳሩ ዜና ህይወታቸውን መዝግባ በየእለቱ የምታስባቸው በተሰየሙበት ተልእኮ ቀጥ ብለው ህዝብን አገልግለው ላለፉ እንደ መምሬ አሰፋ ያሉት ናቸው። የተጠራለትንና የተየሰመለትን ቅዱስ ተልእኮ ፈጽሞ "መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ሩጫየንም ጨርሻለሁ ሃይማኖቴን ጠብቄአለሁ ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፡ ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያስረክበኛል"(፪ኛ ጢሞ ፬፡፯)። የሚለውን ሀዋርያዊ ትዊፊት በተግባሩና በተናገረው እንደዚህ መስክሮ ማለፍ ምንኛ መታደል ነው?

<u>በአዋሳ ቅዱስ ገብርኤል</u> <u>ቤተ መቅደስ ውስጥ የሰው አካል እንዲቀበርበት የተዘጋጀ መቃብር ካለ፡ የሰጠው አገልግሎት ከመምሬ አሰፋ አገልግሎት ጋራ ተወዳደሮ ያሸነፈ ተልእኮ ያለው ቅዱስ ሊሆን ይገባል።</u> እግዚአብሄር መምሬ አሰፋን የሚተካ ካህን እንዲያዘጋጅላቸው "እንብር ለነ ዴበ መንበሩ ህየንቴሁ ኖላዊ ሄር" እያሉ በመጸለይ ላይ ያሉትን የአዋሳን ህዝበ ክርስቲያን በጸሎት እናስባቸው።

በተረፈ ባብነቱ ያዘገጀሁትን ቅኔ ሰምተውና ተረድተው ይበል የሚሉ እንደ መልአከ ምህረት ጳውሎስ ቀጸላ ያሉት ቈጥራቸው በማነሱ፡ ሁሉም በሚሰማው በኢትዮጵያዊው ግጥም ስልት ባመረኛ ባዘጋጅኋት ቅኔ(ግጥም) <u>እግዚአብሔር በጽዮን ከተማ ከመምሬ አሰፋ ጋራ ያገናኘን</u> እያልኩ ሰሚዎቼን እሰናበታለሁ።

# ፫ኛ፡ አማረኛ ቅኔ

## <u>ከልጃቸው ከቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ለተዝካራቸው (ለመታሰቢያቸው) የተዘጋጀች የአማሪኛ ቅኔ</u>

### <u>ስለ ግጥሙ የተሰጠ ማስገንዘቢያ</u>

ኢትዮጵያዊ ቅኔ ወይም አማረኛ ግጥም ከምዕራቡ ዓለም ቅኔ (ግጥም) ቢያንስ በሁለት ነገሮች ይለያል።

፩ኛ፡ የቅኔው ምክንያት ወቅታዊው ክስተት ሲሆን ወቅታዊው መንደርደሪያውን በተሸከመው በመጀመሪያው ክፍል ይካተታል። አሰረ ንጉሥ ወይም ለዓለም በሚባለው በሁለተኛው ክፍል አካባቢውን እየዳሰሰ በመንፈሳዊውም ሆነ በሥጋዊው አመራር ላይ ምስጋና ወይም ተግሳጽ መሰንዘር አለበት።

፪ኛ፡ የግዕዝ ቅኔ፡ በግእዙ ተመጥኖ በተዘጋጀው ባብነቱ ዜማ ልክ መሰፈር አለበት። ከዜማው መስፈርት ከፍ ወይም ዝቅ ካለ፡ ምሥጢሩ ሰምሮ ይበል ቢአሰኝም ዜማ ሰብሯልና ቅኔው ውድቅ ነው። ያመረኛ ግጥም ከሆነ ደግሞ በመሰንቆ በበገናና በክራር ማንም ቢጫወተው መስማማት መቻል አለበት። የማይስማማ ከሆነ ግን ግጥሙ የተሸከመው ምሥጢር ሰሚውን ወሸው ቢያሰኝም፡ ኢትዮጵያዊውን የዘፈን የእንጉርጉሮና የቅራርቶ(ሽለላ) ሰብሯልና ውድቅ ነው።

በቅኔው ሀሰት ወይም ሸፍጥ ከገባበትም ነውር ነው። የሰውን ቅኔ ከራስ እንደመነጨ አርጎ ማቅረብም እጅግ ያስነቅፋል። አንዳንድ ጊዜ የሚዘጋጁ ቅኔዎች በንባብ ወይም በምሥጢር ቀደሞ ከተደረሱት ቅኔዎች ወይም ግጥሞች ጋራ ሊገጥሙ ይችላሉ። የቅኔ ሊቃውንት ባላቸው ልምድና ችሎታ አጀማመራቸውንና አፈጻጸማቸውን በጥንቃቄ ይመለከታሉ። አቅራቢው ስለ ቀድሞው ቅኔ ምንም ግንዛቤ እንደሌለውና ባጋጣሚና ድንገታዊ የፈጠራ ችሎታው የተወራረሰበት መሆኑን ከተገነዘቡ፤ የቀረበው ቅኔ ሆን ተብሎ እንዳልተሰረቀ ተቆጥሮ ተቀባይነት ይሰጠዋል። ሆን ብሎ የሰው ቅኔ የራሱ አስመስሎ ካቀረበ ግን ከውርደቱ ቁስል ጋራ ዘላለም ይኖራታል።

ለመምሬ አሰፋ መታሰቢያ የተጋጀች ይህች ያማረኛ ቅኔ ማንም አማረኛ አንብቦ ሊረዳው በሚችለው መንገድ የተዘጋጀች ናት። እንደ ግእዙ ከውስጠ ወይራ ከውስ ጠዘና ከህብር (ከድሮ ግጥሞች) በጣም ዝቅ ያለ ሰማሰምና ወርቃወርቅ ግጥም ነው። ግጥሙ ወቅታዊውን የመምሬ አሰፋን ክህነታዊ ታሪክ መንደርደሪያ (መነሻ) ቢያደርግም፤ ዘመናት ካለፉ በኋላ ምርምር ማድረግ ለሚፈልጉ ሰዎች በወቅቱ የተፈጸመውን ሁሉ ትዝታዎች አካቶና አቅፎ የያዘ ነው።

## የግጥሙ ይዘት፡-

የመምሬ አሰፋን ማንነትና የተወለዱባት አገራቸው እምን ላይ ሆና በሞት እንደተሰናበቷትና ለ፳፰ ዘመን ያገለገሏትን ቤተ ክርስቲያን ጥለዋት ሲሄዱ በከፋ ሀውክ ላይ እንደነበረችና በሃላፊነት የሚሰየሙት ብዙዎቹ ቅኔ መቀኘት ቀርቶ ግእዙን ማንበብ እንኳ እንደማይችሉ የሚያሳይ ነው። ወፎች የተጠቀሱት የቀብራቸውን ክንውን የሚያሳየው ቪድዮ ርደተ መቃብራቸው ሲፈጸም ያሰሙትን ጫጫታ ለማካተት ነው።

በዚህ ግጥም የተጠቀሱት መልአከ ምህረት ቀጸላ ናቸው። መልአከ ምህረት ጳውሎስ እኔ ተወልጄ ባደኩበት ደብር በመላ ኢትዮጵያ ተደናቂ የነበረውን የመሪጌታ ውብሸትን ቅኔ ለመማር ከተወለደበት ደብር መጡ። በወቅቱ መሪጌታ ውብሸትን ተከተው ያስተምሩ ከነበሩት በኋላ ቅኔ ማስተማሩን ትተው ዘመናዊ ትምህርት ተምረው የመብራት ሃይል ድርጅት ባልደረባ ሆነው አገራቸውን ሲያገለግሉ ከኖሩ በኋላ በቅርቡ ለህክምና አትላንታ መጥው ያረፉት መሪጌታ በላይ ውብሸት ነበሩ። መልአከ ምህረት

ጳውሎስ ከሳቸው ጉባዔ ቅኔውን የተማሩ ናቸው። በኋላም ወደ አዲስ አበባ ተሻግረው ከመምህር ቀጸላ በኋላ አቡነ እንድርያስ ከተባሉት ሊቅ ያብነቱን ትርጓሜ ተምረው በመጨረስ የመጽሀፍ መምህር ናቸው።

በ፲፱፻፷፰ የሰበካና የስብከት ክፍል ኃላፊ ሆኘ ወደ አዋሳ ተልኬ ፪ አመታት በቆየሁበት ወቅት የአዋሳ ደብር አለቃና የሲዳሞ ሀገረ ስብከት ሰባኬ ወንጌል ነበሩ። ከዚያ ቦታ በግምት ለ፵ አመታት ያህል በአገልግሎት ላይ ከመምሬ አሰፋ ጋራ አብረው ኖረዋል። በደብሩ ለምስክር ያህል አሁን ከሞቱትም ሆነ እኔን ጨምሮ በህይወተ ሥጋ እያለን ከተበታተነው በአዋስ ከተማ እሳቸው ብቻ ለምስክርነት መቅረታቸውን ያሳያል። የቅኔውን ደራሲ እኔን ማለቴ ነው ይህን ግጥም ሳዘጋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ አለመኖሬንም ያመለክታል።

## የግጥሙ መነሻ (መንደርደያ)

በትንሳኤ አምናለሁ እኔ አልቀርጥም ተስፋ
እንደ ሞተ አድርጌ ጨርሶ እንደጠፋ
ቁጭ ብየ አላለቅስም ለመምሬ አሰፋ።

ቅኔውን በግእዝ አልቀኝልህም
አንተ እያንቀላፋህ አታርምልኝም
አልናገረውም ቅኔየን ለማንም
ዝረፍ ዝረፍ እንጅ ይበል የሚል የለም።

በእንቅልፍ ላይ ሆነህ ቅኔየን ባትሰማ
ክርስቶስ ቀስቅሶህ ሲመለስ በግርማ
ታርምልኛለህ በጽዮን ከተማ ።

## አሰረ ንጉሥ (በወቅቱ የሚንጸባረቁ ክስተቶች)

አንድ ሰው ካስመራ ጌሾ አምጥቶላት
ዋርሰዋ ካድዋ ብቅል አቅርቦላት።

ያቺ ዘላኗ ሴት ያረገችው ጠላ
የጠጣውን ሁሉ እርሱ በእርሱ አባላ።

ያን እየጠጣችሁ ሰዎች አትስከሩ
በሰውዬው ጠፍር እንዳትታሰሩ።

አቡኖች ነበሩ የህዝብ አስታራቂ
ከሰውዬው ጋራ እየጠጡ አረቂ።

እስ በሱ ተናክሰው ተባልተው አለቁ
የተጣላውን ህዝብ እንኳን ሊያስታርቁ።

ሁኔታቸው ገርሞኝ ቆሜያለሁ በሩቁ
ሰምና ወርቅ ቅኔ ውስጠ ወይራ አያውቁ
በወርቃ ወርቅ ቅኔ እየተራቀቁ
ተናንቀው ሊያልቁ ነው እየተናጠቁ።

አልቀኝም ቅኔ አልጽፍም ጦማር
መኮንን አሰፋ ከሌለ ባገር
የሚያርመኝ የለም ምሥጢሩ እንዲሰምር።

የኛ መነኮሳት ሄዱ እየረቀቁ
ቅኔ መቁጠር ትተው ብር መቁጠር አወቁ
ከገዳማት ወጡ እየተመረቁ።

አገር የሚፈቱ ጳጳሳት ሳሉት
እየተላቀሱ ወፎቹ ፈቱት።

መሬቱ ተናውጦ ሲደፈርስ ምንጩ
ነፋሱ ገፍቷቸው ሰዎቹ ሲጋጩ
ዛፍ ላይ የሰፈሩት ወፎቹ ተንጫጩ።

በሀገራችን ላይ የተነሳው ነፋስ
ገለበው ሁሉንም አስቀረው ያለ ልብስ።

ገለባ ሆነና ሁሉም ተንሳፈፈ
ጵጵስናው ሳይቀር እንደወፍ ከነፈ።

ጵጵስናው ሲከንፍ ሰዎቹ ጨንቋቸው
ና ና ውረድ አሉት ያረገ መስሏቸው።

ባለመቀበሬ በራሴ ባድማ
ሬሳ ነፋጊ ተብየ ልታማ።

አይጠራ ስሜ ታሪኬም ይረሳ
አልመኝላትም ለኢትዮጵያ ሬሳ።

ሥጋየንም ብሉት ደሜንም ጠጡት
ነፍሴን አላስነካም ለፈጣሪ ናት
ኢትዮጵያዊነቴ ለኔ ነፍሴ ናት።

ድንጋዩን ቀቅሉት ከበሰለላችሁ
አሸዋውን ፍጩት ከደቀቀላችሁ
ሁሉንም ጉረሱት ከተዋጣላችሁ
አትብሏት ኢትዮጵያን እየቆረሳችሁ
በሞሰብ ላይ ያለች እንጀራ መስላችሁ።

ምስጥ ሁሉን ይበላል ምንም ሳይቀረው
እርሱ በርሱ አይባላም ደም ስለሌለው።

ሁሉም ምስጥ አንድ ነው ሰውነት አያውቅም
ምስጥ አወዳድሬ ያገሬን አልመርጥም
ለኢትዮጵያ ምስጥ ሥጋየን አልሰጥም ።

መምሬ አሰፋ ሆይ አንተ ታላቅ መምህር
ተመለስ አትበለኝ ወደ አገርህ ምድር
ወፎች ካለቀሱ ሰው በሰው ሲቀበር
በርሬ እንዳሞራ እንደወጣሁ ልቅር።

አጽመ ርስት ከሌለኝ ከተሸጠ እትብቴ
በኢትዮጵያ ምድር አይሰራ ቤቴ።

ሰዎች ዝም አትበሉ ጥያቄ መልሱ
ጥቅሙ እምን ላይ ይሆን ካገር መመለሱ
ሰውን ሰው ሲቀብረው ወፎች ካለቀሱ?።

## <u>የግጥሙ ምንጭ (መንደርደ)</u>

እንዳንተ አልበቃሁም ለትልቁ ማዕረግ
ሰው ከሰው ሲራራቅ ሁሉም ሲበረግግ
ወፎችን አውቄ ጓደኛ ለማድረግ።

የሰው ሁሉ ማበድ አድርጎህ ብቸኛ
አንተን አደረግህ የወፎች ጓደኛ።

ሳልመለስ ብቀር እንዳትፈርድ በኔ
አላስተማርከኝም የወፎችን ቅኔ።

ማን ያጫውተኛል ስሜቴን ተረድቶ
ሰው ሁሉ ካበደ ከራሱ ተጣልቶ።

ይቅርታ አድርግልኝ አንተ ትልቅ ካህን
ባለመመለሴ ሰምቼ ቃልህን ።

እንዳትቀየመኝ እኔ አልመለስም
በሰዎች ስቀበር ወፍ አላስለቅስም።

አገር አለኝ ብሎ ወደ አገር የሄደ
ከራሱ ተጣልቶ እንደዚህ ካበደ
መቅረት ይሻለዋል እንደተሰደደ።

ወፎች የተንጫጩት ቄሶች ሲቀድሱ
ሰውን ታዝበው ነው ተሸለው እነሱ
የጨው ካብ ተንዶ ብልሆች ሲያለቅሱ
እነ ሆድ አምልኩን አዩአቸው ሲልሱ።

ግንዘቱ ተነቦ ካህኑ ሲቀበር
ወፎች የተቀኙት ምሥጢሩ ምን ነበር?

የተቀኙት ቅኔ ግሩም ነው ምሥጢሩ
ተርጓሚ አላጠፋም ጭራሽ ከሐገሩ
አንድ ሰው ብቻውን የሚኖር በደብሩ
እሱ ይንገራችሁ ምሥጢሩን ባጭሩ።

ቅኔውን ተርጉሜ እኔ እንዳልነገራችሁ
አትመጡ ወደኔ እኔ አልደርስባችሁ።

ትርጉሙን ለማወቅ ፍላጎት ያላችሁ
ጳውሎስ ቀጳላን ጠይቁ እባካችሁ።

ምሥጢሩን ያውቀዋል ጳውሎስ ቀጳላ
ይህን ሊነግራችሁ ቀርቷል ወደ ኋላ።

ምሥጢሩን ደብቆ እንዳያመልጣችሁ
ጳውሎስ ቀጳላን ያዙት አጥብቃችሁ።

አትውቀሱ አባቴን ጠፋብን ብላችሁ
ብቻችሁን አርጎ አልሄደም ጥሏችሁ
ከጳውሎስ ጋራ ወፎች አሉላችሁ።

እንዳረመኔ ሰው እንደሌለው ተስፋ
ማልቀሱን አቁሙ ለመምሬ አሰፋ።

ወንጌሉ ያዝዛል ሰው ለራሱ እንዲያለቅስ
የተበታተነው እስኪገናኝ ድረስ።

ለራሴ አለቅሳለሁ አሜሪካ ሆኘ
ሁሉም የሞተ ነው ሰው ካልተገናኘ።

በተፈጠርንባት ባደግንባት ምድር
በነገረ ሰሪ ሳንገናኝ ብንቀር
አምላክ ያገናኘን በላይኛው አገር።